## የአዛኝ ቅቤ አንጓችነት ወይንስ አህያውን ፈርተው ዳውላውን?

የአገራችን የፖለቲካ ምህዋር ቅጥ አንባሩ ጠፍቶ የምንይዝ የምንጨብጠውን አጥተን የዕውር የድንብር መጓዝ ከጀመርን ውለን አድረናል:: ለዚህ ወግ የለሽና መቋጫ ያጣ የተቃዋሚ ነን ባዮች የትግል ጉዞ የወያኔንን መንግሥት ተጠያቂ ማድረግ የዚህን ጎጠኛ ቡድን ሰይጣናዊ ባህሪ መግለጽ ሳይሆን ምንም የሚሳነው የለውም ብሎ ማሞካሸት ነው የሚሆነው::

በእኔ እምነት ወያኔ በሰይጣናዊ ተግባሩ የተንኮል ቋጠሮ ይሁን እንጂ በራሱ ሰይጣን ወይንም አብነት ኖሮት ባለንበት ሁሉ ተገኝቶ ሊያሰናክለን አይችልም:: ስለሆነም 19 ዓመት ሙሉ ረግጦ እየገዛን ያለው በበጎም ሆነ በተንኮል ብቃቱ ሳይሆን በኛው ተቃዋሚ ነን ባዮች ራስ ወዳድነትና የምቀኝነት የትግል አካሄድ ነው:: ይህንን አስመልክቶ የተከበሩ ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ በአውስትራሊያ የሥራ ጉብኚታቸው ወቅት ስለ አንዲት የባሕር ውስጥ እንሰሳ ስለክሬፐስ እንደምሳሌ አድርገው ሲናገሩ „ክሬፐስን አንድ ብቻዋን በርሚል ውስጥ ብትተዋት ተመልሰህ አታገኛትም ነገር ግን ሁለት ሶስት አድረገህ ብትተዋቸው ዬትም አይሄዱም፣ እዚያው እርስ በርስ ሲጓተቱ እንዳሉ ታገኛቸዋለህ ብለው“ ነበር:: እኚህ ምሁር ይህንን ምሳሌ የተጠቀሙት ያለምክንያት አልነበረም:: እንዲህ ዓይነቱን ትምህርታዊ ንግግር ሲያደርጉ የመጀመሪያቸውም አይደለም:: ካሁን በፊትም በተለያዩ አጋጣሚዎች ወሬ ትተን የምንደግፈውን ኢትዮጵያዊና ጸረ ወያኔ ድርጅት በተግባር እንደግፍ ሲሉ ተደምጠዋል::

ይሁን እንጂ ይህንን የተናገሩትን ሀቅ እርሳቸው የሚመሩትን G7 የሚደግፉና በድርጅቱ ውስጥ አባል ሆነው የሚንቀሳቀሱ ምንም እንኳን ዛሬ በትግል ስልት ብንለያይ ለአንድ ዓላማ የምንታገል የትግል አጋሮቻችን ናቸው ብለን እምነት የምንጥልባቸው ዎንድሞቻችንና እህቶቻችን ባንድ በኩል ወይዘሪት ብርቱካንን የደገፉ በመምሰል የአዞ እንባ ሲያነቡ በሌላ በኩል ግን እርሳቸው የመሰረቱትን ድርጅት ለማፍረስ በካረንት አፌይርስ (Ethiopian Current Affairs) አድሚኖች ጠቅላላ ስብሰባ ውሳኔ ተላልፎ በተቀናጀ መልኩ ዘመቻ በማካሄድ ላይ መሆናቸው የአዛኝ ቅቤ አንጓች መሆን ብቻ ሳይሆን የጸረ ወያኔው የትግል መስመር ወዴት እየተገፋ ነው የሚል ጥያቄ እየጫረብን ይገኛል::

ይህንን ቅሬታዬን ስገልጽ ካረንት አፌርስ የአንድ ድርጅት መሳሪያ ሳይሆን ራሱን ችሎ በቦርድ የሚንቀሳቀስ የማስ ሚዲያ አካል መሆኑን ዘንግቼ አይደለም:: ሆኖም ግን የ G7 ህቡዕ የአባላት ተሳትፎና ዝርዝር አያያዝ የተጠበቀ ሆኖ ካሁን በፊት ከነበረን ቅርበት በደንብ የትና በምን የስራ ድርሻ ድርጅቱን እንደሚደግፉ የምናውቃቸው፣ ከበሬታም የምንሰጣቸው ወገኖቻችን ከባልሽ ባሌ ይበልጣል … ይሁን ወይም በሌላ በማናውቀው ምክንያት በድርጅታችን ላይ የጀመሩትን አፍራሽ ዘመቻ በመቀጠል የድጋፍ ድርጅቶችን ጭምር የስድብ ውርጅብኝ ሲያዘንቡ ውለው ያድራሉ:: ለአብነት „የአደራ ሬዲዮ“ አንድ ሳምንት የፈጀ ጥናታዊ ጽሁፍ ተብሎ በጉዱ ካሳ የቀረበውን ስድብና ዛቻ መጥቀሱ ይበቃል::

ይህ ቤት በአገራችንና በሕዝባችን ጉዳዮች ዙሪያ ተወያይቶ ገንቢ ሀሳቦችን ከማቅረብ ባሻገር በቁሳዊ ድጋፉም የታወቀ መሆኑን በሚገባ እረዳለሁ፣ ብዙ ምሁራኖች የሚሳተፉበትና ትልቅ ትምህርት መቅሰሚያ መድረክም ነው ብዬ አምናለሁ:: በአንጻሩም ደግሞ የበግ ለምድ የለበሱ ተኩላዎችም አፍራሽ ተልዕኮአቸውን የሚያከናውኑበት፣ የዋሆች ማናጀ የሚሆኑበትና አንዳንድ ስራ ፈቶችና የወሬ ሱስ ያለባቸው መደበሪያቸው መሆኑንም እገነዘባለሁ:: ሆኖም ግን በአገራችን እንደ ሰማይ የራቀውን የመናገር መብት በግላጭ አገኘነው ብለን የምንበቀለው ይመስል ግዴታን ያላካተተ የሌላውን መብት በሚነካና ትግሉን በሚጎዳ መልኩ እየተካሄደ ያለው ዘመቻ ይህ ቤት እንኳን ባለቤት ያለውና በቦርድ የሚመራ ቀርቶ ቢያንስ የሞራል ተጠያቂነት እንኳ ያለው አይመስልም::

ይህ በአንድነት ፓርቲና በደጋፍ ድርጅቶቹ ላይ የተከፈተው ወረራ ወዳጅና ጠላትን ለይቶ አለማየት ዘመቻ የሚጎዳን እኛኑ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::

ሁሉም ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች የሚበጃቸዉን የትግል ስልት መርጠዉ ታክቲክና አስትራቴጂ ነድፈዉ በመንቀሳቀስ ላይ ስለሆኑ እኛም ያመንበትን ድርጅት በተግባር መደገፍ፣ የአካሄድ ስህተት አለ ብለን ካመንም አግባብ ባለዉ የግንኙነት መስመር መፍትሄ ለመሻት መሞከር፤ ያ ካልሆነ ከድርጅቱ ጋር ወደፊት ሊኖረ በሚገባዉ ግንኙነት ላይ የግሉን መወሰን ብልህነትና ስልጡን አካሄድ ይመስለኛል እንጂ እኔ ያልኩት ካልሆነ ብሎ ጋሪዉን ከፈረሱ ለማስቀደም መሞከር አግባብ አይመስለኝም::

በተቃዋሚ ድርጅት መሪ ነን ባዮች የስልጣን ጥማትና የአመራር ጉድለት የምንደግፋቸዉና እምነት የጣልንባቸዉ ድርጅቶች ከጠበቅነዉ ዉጭ ሆነዉ በማየታችን አንዳንድ ቀና የሆኑ ዎንድሞቼና እህቶቼ ከብሶት የመነጨ እሮሮ ሊያሰሙ ብችሉም ጊዜና ቦታዉን ያልጠበቀ ወዳጅና ጠላትን ያለየ በአንድነት ፓርቲ ላይ ዘመቻ መክፈት የጠላትን ጎራ ማጎልበትና ወዳጅን ማዳከም አለዚያም አህያዉን ፈርቶ ዳዉላዉን ነዉ የሚሆነዉ::

ይህቺን የዉስጥ ስሜቴን ገሀድ ለማድረግ የተገደድኩት እኔ የምደግፈዉን አንድነት ፓርቲ ይህ ከዲአስፖራ የተከፈተበት አፍራሽ ዘመቻ አገር ቤት በሚያኪያሂደዉ ትግል ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያመጣል የሚል ስጋት ኖሮብኝ ሳይሆን ድርጊቱ ለአገርም ሆነ ለሕዝብ ብሎም እያንዳንዱ እደግፋለሁ ለሚለዉ ድርጅት የሚሰጠዉ ጠቀሜታ ስለሌለዉ ነዉ::

ለተቃዉሞዉ መንስኤና የሚሰጡ ምክንያቶች:-

1. ሰላማዊ ትግል ኢትዮጵያ ዉስጥ የለም ማካሄድም አይቻልም

2. አንድነት ፓርቲ መሪዉን አሳስሮ ዝም ብሏል

3. ፓርቲዉ መድረክን መቀላቀሉ አግባብ አይደለም

4. ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳና አቶ ስየ አብርሃ የአንድነት አባል ብሎም አመራር ቦታ መያዛቸዉ አግባብ አይደለም እና ሌሎች ተጓዳኝ ምክንያቶች ናቸዉ

እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን አራት ዋና ዋና ምክንያቶችን አጠር ባለ መልኩ ለማሳየት እሞክራለሁ::

(1) ሰላማዊ ትግል ለኢትዮጵያ አይሰራም ማካሄድም አይቻልም ከሚል ድምዳሜ የተደረሰዉ የወያኔ መንግሥት ከ30 ዓመት ያላነሰ ጊዜ ታግሎ በጠብመንጃ አፈሙዝ ያገኘዉን ስልጣንና የግል ጥቅም እንዲሁ በዋዛና ፈዛዛ ያስረክባል ብሎ ከመጠበቅ ከሆነ በጣም የዋህነት ነዉ:: አሊያም በሰላማዊ መንገድ የስልጣን ሽግግር ይደረጋል ሲባል እንደ ዱላ ቅብብሎሽ አንዱ የተወሰነ ቦታ ካደረሰ በኋላ በገዛ ፈቃዱ ለሚቀጥለዉ አሳልፎ የሚሰጠዉ ነገር ተደርጎ ተወስዶም ከሆነ የግንዛቤ ጉድለትን ያንፀባርቃል:: ምክንያቱም እንኳንስ ለዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ባዕድ ሆነን የቆየን ኢትዮጵያዉያን ቀርተን ከስርአቱ ጋር የቆየ ትስስር ያላቸዉ የበለጸጉ አገሮች ዉስጥ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር የሚደረገዉ በበቃኝና በፍላጎት ሳይሆን መራጩን ሕዝብ ለማሳመን ከፍተኛ ወጪና ተጋድሎ በማድረግ ነዉ::

በእንደኛ አይነቱ በአምባገነኖች ተረግጦ ለሚገዛ ሕዝብ ሥልጣን በሰላም እንዲተላለፍ ለመድረግ ከፍተኛ መስዋዕትነትና ትእግስትን ይጠይቃል:: ይህም የሚሆነዉ አንደኛ መንግሥት ተብሎ በመሳሪያ ሀይል የሚገዛ ሁሉንም የስልጣን ተዋረድ አማክሎ የያዘ በመሆኑ ማንኛዉንም በጥቅሙና በስልጣኑ የሚመጣዉን ያለ ምንም ርህራሄ የመጨፍለቅ ሀይል ስላለዉ ማንኛዉንም የሰላማዊ ትግል ስልቶችንና ሕዝቡን በቅጡ ሳያደራጁ፣ መብትና ግዴታዉን አዉቆ በቆራጥነት እነደሚሰለፍ ሳያረጋግጡ ተግባራዊ ለማድረግ መጣደፉ ዘለቄታ ያለዉን መፍትሔ ያመጣል የሚል እምነት የለኝም (የ97ቱ ምርጫ ሕዝባዊ ድልና ዉጤቱንም ማስከበር አለመቻልን ያጤኗል):: መብትና ግዴታን አዉቆ፣ በዓላማ ጸንቶ ከግል ጥቅምና ዝና ለሕዝብና ለሀገር ልዕልና ቆርጠዉ የሚታገሉ እንደ ወይዘሪት ብርቱካን አይነት መሪዎችን ለማግኘት በየድርጅቶችና ድርጅት ከድርጅት ጋር በሚያደርገዉ ፍትጊያ የግል ጥቅም

የሚያማልለዉ እየተራገፈ ቀራጥና በአላማዉ የጸና እየተቀናጀ እስከሚመጣ ጊዜ መጠየቁን መረዳትም ተገቢ ይመስለኛል::

ከሁሉ በላይ ሰላማዊ ትግሉን የሚጻረሩ ነገር ግን ለዚያች አገርና ሕዝብ የሚጨነቁ ወገኖቼ አማራጭ ነዉ ብለዉ የሚያስቀምጡት የትጥቅ ትግልን ነዉ:: እኔ ምርጫቸዉን አልቃወምም፣ መብታቸዉም ነዉ:: የማይገባኝ ነገር ቢኖር - የትጥቅ ትግሉን የመረጡ ወገኖቼ ወያኔን በሚያዉቀዉ ቋንቋ እናነጋግራዉ ብለዉ እስከተነሱ ድረስ ጠብመንጃቸዉም ፕሮፓጋንዳቸዉም ማነጣጠርና ማነጋገር ያለበት ወያኔን መሆን ሲገባዉ አንድነትን መደብደቡ አህያዉን ፈርተዉ ከምኑም ያልደረሰዉን ዳዉላ መደብደብ አይሆንም ወይ? የጋራ ጠላታችንን ትቶ ገንዘብና ጉልበትን 24 ሰዓት ማይክራፎን ላይ ተቀምጦ አንድነትን በመሳደብና የድጋፍ ድርጅቶችን ለማዳከም ጊዜንና ኃይልን ማባከን ጠቃሚነቱ ለማን ነዉ?

እኔ የትጥቅ ትግልን የማልደግፈዉና በትጥቅ ትግል ዲሞክራሲያዊ የሆነን ሥርአት ማምጣት ይቻላል ብዬ ባላምንም ሁሉም መሳሪያ ያነሱት ወይንም የትጥቅ ትግልን የመረጡት ለምሳሌም እንደ ጂ7 አይነቱ በወያኔ መንግሥት አስገዳጅነት ተገፍተዉ ይህንን መስመር የተከተሉ መሆናቸዉን ስለምረዳ እኔ የምደግፈዉን መስመርና ድርጅት ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ከመደገፍ አልፌ በሌሎቹ መንገድ ላይ የእንቅፋት ድንጋይ መኮልኮል አልፈልግም:: ሌላዉም እንዲህ ቢያደረግ ባንዱ ያጣነዉን ድል በሌላዉ እናገኛለን የሚል እምነት አለኝ::

(2) አንድነት ፓርቲ መሪዉን አሳሰሮ ዝም ብሏል:-

ድርጅቱ መሪዉን አሳስሮ ለማስፈታት የሚያደርገዉ ጥርት የለም፣ የመሪዋን መፈታት እንደ ቅድሜ ሁኔታ አድርጎ ምርጫዉን ላለመሳትፍ መወሰን ነበረበት የሚሉ ክፍሎች አሉ:: ብርቱካን ይዛ የተነሳችዉ ዓላማ ሕዝባዊና አገር አቀፍ በመሆኑ ለብርቱካን መፈታት መታገል ያለበት የአንድነት ፓርቲ አመራር፣ አባላትና የፓርቲዉ ደጋፊዎች ብቻ ናቸዉ እንጂ ሌላዉን ምን ያገባዋል የሚል አስተሳሰብ የለኝም:: ሆኖም ግን አገር ቤት ያለዉን ነባራዊ ሁኔታን ባላገናዘበ መልኩ ድርጅቱ መሪዋ እንድትፈታ እየተደረገ ያለዉን ሁሉ አቀፍ ሙከራ ከምንም ሳይቆጥሩ ለመታሰሯ ሁሉ ምክንያት የሆኑ ይመስል “አሳስረዋት“ እየተባለ ሲነገር መስማቱ እጅግ የሚያሳዝን ነዉ:: ብርቱካን የሁላችንም ነች ካልን ለማስፈታት እኔ ምን አደረኩ ወይንም በነጻዉ አለም የምንኖር እኛስ ምን አደረግን ብለን እራሳችንን መጠየቅ ነበረብን::

ሌላዉ አንድ የተደራጀ ለአገርና ለወገን የተሻለ ራዕይ አለኝ ብሎ የተነሳን የፖለቲካ ድርጅት የአካሄድ ስህተት ሲፈጽም መስመር ሲለቅ ወደ ፈሩ እንዲመለስ ገንቢ ሂስ ማቅረብ በጣም ተፈላጊ ነዉ:: ነገር ግን ሂስ ገንቢ የሚሆነዉ ጊዜና ቦታዉን ጠብቆ፣ ስህተትን በተጨባጭ መረጃ አስደግፎና መፍትሄዉን የሚያመላክት ሲሆን ብቻ ነዉ:: ከዚህ ዉጭ የሚደረግ መሰረተቢስ ስድብና ወረራ አንድም ዶክተር ብርሀኑ ነጋ እንዳሉት „የምቀኝነት“ ተግባር ነዉ አሊያም አንድነትን ለማፍረስ የሚደረግ የሰርጎገቦች ደባ ነዉ የሚሆነዉ::

የፓርቲዉን በምርጫ መሳተፍን አስመልክቶ የሚነዙ ዉዥንብሮችን የድርጅቱ አመራሮች በተለያዩ ሚዲያዎች ተጋብዘዉ አቋማቸዉን ግልጽ አድርገዋል:: ይሄዉም ፓርቲያቸዉ የምርጫ ፓርቲ መሆኑን፣ ነገር ግን በምርጫ የሚሳተፉት በማናጀነት ሳይሆን ምርጫዉ ፍትኃዊና የመወዳደሪያዉ ምህዳር የሰፋ ከሆነ ብቻ መሆኑን አረጋግጠዋል:: ከዚያ ዉጪ ወይዘሪት ብርቱካን በአዉሮፓዉ ጉብኚታቸዉ ወቅት በምንም አይነት ሜዳዉን ለወያኔ ብቻ አንለቅም ባሉት መሰረት መሟላት የሚገባቸዉ ነገሮች እንዲሟሉ ጥረት እያደረጉ ሁኔታዎች ተመቻችተዉ ለምርጫ ቢቀርቡ ዉጤት እንዲኖረዉ መደረግ የሚገባቸዉን ቅደመ ሁኔታዎችን ከወዲሁ ማመቻቸት ብልህነት እንጂ የሚያስወቅሰ ሊሆን አይችልም::

(3) ፓርቲዉ መድረክን መቀላቀሉ አግባብ አይደለም

በመሰረቱ የአንድነት ፓርቲ መድረክን የመቀላቀል ተግባር የተጸነሰዉና የተጀመረዉ ከወይዘሪት ብርቱካን መታሰር በኋላ አይደለም:: እርሳቸዉ ከመታሰራቸዉ በፊት የተጀመረዉን ተግባራዊ አደረጉት እንጂ:: ወይዘሪት ብርቱካን የአንድነት ፓርቲ መስራችና የድርጅቱ ሊቀመንበር ናቸዉ:: ስለሆነም ስለ አንድ የፖለቲካ ድርጅት ትክክለኛነትና ስህተት ስናወሳ ስለመሪዉ የአመራር ብቃት ነዉ የምናወሳው:: ስለ መሪዉ የአመራር ብቃት ሰናነሳ ደግሞ ስለ ድርጅቱ የመስመር ጥራትና የአካሄድ ብቃት ነዉ:: ብርቱካንን የደገፉ መስለዉ ፓርቲዋን የሚያንኳስሱ የአዛኝ ቅቤ አንጓች እንጂ እዉነተኛ ተቆርቋሪ ሊሆኑ አይችሉም::

ግንዛቤአችን እየፈጩ ጥሬ ካልሆነ በቀር አንድነት መድረክን መቀላቀሉ የነበረንን ኢትዮጵያዊ አንድነትና ትስስር፣ ነገር ግን ለ20 አመታት በወያኔ ተንኮል አጥተነዉ የነበረዉን ከማደስ ባሻገርና የጎጥ ፖለቲካን መሰረት ከማሳጣት በቀር የሚያስከትለዉ ችግር ያለ አይመስለኝም:: መድረክ የስምንት የተለያዩ ራዕይ ያላቸዉ ፓርቲዎች ስብስብ ሲሆን የየግል ራዕያቸዉን ሰጥቶ በመቀበል መርህ አንድ በሚያደርጋቸዉ ጉዳዮች ተስማምተዉ በኢትዮጵያ አንድነት ስር አብሮ ለመኖርና ለማደግ ቅድመ ሁኔታዎችን ማመቻቸቱ ያስመሰግነዋል እንጂ ሊያስወቅሰዉ አይገባም:

(4) ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳና አቶ ሰየ አብረሀ የአንድነት ፓርቲ አባል መሆንና የአመራር ቦታ መያዛቸዉ አግባብ አይደለም እና ሌሎች ተጓዳኝ ምክንያቶች ናቸዉ እነኚህ ሁለት ታዋቂ ግለሰቦች ካሁን በፊት በወያኔ መንግሥት ስር በነበራቸዉ ተሳትፎና ሃላፊነት ይህ ጎጠኛ መንግሥት በፈጸማቸዉ ሕዝባዊና አገራዊ ወንጀሎች ሆን ብለዉም ይሁን ከግንዛቤ ጉድለት የሚጋሩት የየራሳቸዉ ድርሻ መኖሩን ይፋ አድርገዋል:: ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ <u>ፎርማሊ</u> አጥፍቻለሁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ ይቅር በለኝ ሲሉ አቶ ሰየ አብረሀ ደግሞ ጥፋት እንዳለ ነገር ግን ከሁኔታና ከጊዜ አኳይ ይቅርታ ጠያቂም አድራጊም እንደማይኖር ገልጸዋል:: እኔ ይቅርታን አስመልክቶ ሁለቱም የሄዱበትን መንገድ በቀና መልኩ ስመለከተዉ የሚያስኬድ ነዉ:: አንደኛዉ ይቅርታዉን የተጠቀመዉ ቢያንስ ለጎሊናዉ ሲልና የቆሰለዉን የሕዝብ ልብ ለማበስና ሊመጣበት የሚችለዉን ወቀሳ ለመቅደም ሲሆን ሁለተኛዉ ጥፋት እንዳለ አምኖ የበደልኩትን ሕዝብ ለመካስ ቀድሞ የተሳተፍኩበት አካሄድ ትክክል ሰላልነበረ ያንን የሚተካ መስመር መርጬ እየታገልሁ ነኝ ከዚህ ዉጪ ሁላችንም ታግለን ሕዝባችንን የስልጣን ምንጭ ካደረግን በኋላ ሕዝቡ የመፍረድም ይቅርታ የማድረግም አቅም ሰለሚኖረዉ ሁላችንም የየድርሻችንን እያነሳን ይቅርታ ብንባባል መልካም ነዉ ባይ ነዉ::

እኔም ያለኝ ግንዛቤ ለዚች አገር ኋላ ቀርነት፣ ረሀብ፣ በሽታና የጦርነት ምንጭ መሆን ተጠያቂ የወያኔ መንግሥትና ደጋፊዎቹ ብቻ ሳይሆኑ ቢያንስ በእኛ ዕድሜ አይተናቸዉ ያለፉት ሁለት መንግሥታትና ደጋፊዎቻቸዉም ጭምር መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል:: ይህንን ሳናደረግ የብዕር ስም አንግበን ማን ያዉቀኛል በሚል ማይክራፎን እያነሳን ማንንም መዘለጥ ስራችን አድርገን የተያያዝን ግለሰቦች ወያኔ ሥልጣን ከጨበጠ በኋላ የተወለድን የ20 ዓመት እድሜ ያለን ግለሰቦች አይደለንም፣ ከደሙ ንጹህ ነኝ ብለን ልንዝናና አይገባንም:: ስለሆነም ከወያኔ ጋር እንኳ ንኪኪ ባይኖረን ባለፉት ሁለት ስርአቶች ለነበረዉ ጥፋት ከተሳታፊነት እስከ አድር ባይ ተመልካችነት ያበረከትነዉ አስተዋጽዖ ያልነበረ ይመስል ባይናችን ዉስጥ ያለዉን ምሰሶ ሳናይ በሰዉ ዐይን ያለዉን ጉድፍ ማየት ችለን ላዉጣልህ ወይንም እንዲህ አድርገህ አዉጣዉ ሳይሆን በዐይኑ ጉድፍ ተሸክሞ ይዞራል ብሎ መስደብና መሳለቁ በጣም የሚያስተዛዝብ ጉዳይ ነዉ የሆነብኝ::

ወያኔ ከኛ ተሽሎ ከጉያችን ሰዎችንም ሆነ ድርጅቶችን በተለያየ መልኩ እያስኮበለለ ሲወስድ በኛ ጥረት ሳይሆን በራሳቸዉ ፍላጎት ወያኔን እየከዱ የሚመጡትን በሙሉ በጠላትነት እየፈረጅን ማባረሩና ባላንጣ ማብዛቱ ደካማነት እንጂ ብልህነት ወይንም ጉብዝና አይደለም:: መጠራጠር ተገቢም ቢሆን ህልም አያለሁ ተብሎ ሳይተኛ እንደማይታደር ሁሉ አብሮ እየሰሩ አካሄዳቸዉን መመልከቱ ተገቢ ሲሆን ሁለቱ ግለሰቦች በፓርቲዉ ዉስጥ ካሉ አባላትና አመራሮች በችሎታ በልጠዉ እንዳሻቸዉ ያደርጋሉ ብሎ መገመቱ መሰረት የሌለዉና ሊታመን የማይችል ፍራቻ ነዉ:: ሌላዉ አስገራሚ ነገር ሰየ አብረሀና ከእርሱ ጋር አብሮ ለመስራት የወሰኑት ከእሳይያስ አፈወርቂና አብረዉት ከሚሰሩት የበለጠ ጠላት የሚሆኑበት ሚስጥርና ከበረሀ ጀምሮ ከሰየ ጋር የራሳቸዉን ብሔረሰብ ሲያስጨርሱ መጥተዉ ወያኔን ለስልጣን ያበቁ ከዚያም በሗላ ሕዝብ ሲጨፈጭፉና ሲያስጨፈጭፉ የነበሩ ትናንትና ወያኔ

መፈንቅለ መንግሥት ሊያካሀዱብኝ ሲሉ ደረስኩባቸው ብሎ ያሰራቸውን ጀግኖቻችን እያሉ እነኚህን በጠላትነት መፈረጅ ራስን በራስ መቃረን አይደለም ወይ?

በእኔ እምነት አንድነት ከመድረክ ጋር አብሮ ለመስራት መወሰኑና መለስተኛ የድርጊት መርሀግብር ነድፈው አብሮ ለመስራት መብቃቱ የወያኔን የጎጥ ፓለቲካ የማክተሚያው ዋዜማ መሆኑን የማመልከቱን ያክል የሁለቱ ግለሰቦች አንድነትን መቀላቀል የትግራይንና የኦሮሞን ሕዝብ አንድነት የነፍጠኛ አማራ ስብስብ ነው ወዮልህ እኛ ከሌለን እናንተም የላችሁም ያጠፏችኋል እያለ ለማስፈራሪያነት የሚጠቀመውን ቅጥፈት ከማምከኑ በተጨማሪ ሰራዊቱን እንደ ደርግ ሰራዊት ሊያጠፉህ ነው እያለ መጠቀሚያ ማድረጉን ቀጣይነት እነዳይኖረው ያደርጋል:: ይህም የሚያመለክተን ወይዘሪት ብርቱካን በአንድ ወቅት አንድነት ጠላት የለውም ያለችውን የሚያረጋግጥና ድርጅቱ የብቀላ ፓርቲ ሳይሆን የጥላቻ ፖለቲካን አስወግዶ አገር አቀፍ እርቅ እንዲኖር የሚታገል ድርጅት መሆኑን ነው::

ውድ አንባቢያን ይህችን አነስተኛ የውስጥ ስሜቴን ልትገልጽልኝ የምትችል ነች ብዬ ያመንኩባትን መጣጥፍ እንድጭር ያስገደደኝ ከላይ ከመግቢያው ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ኢትዮጵያን ካራንት አፌርስ የፓልቶክ ሩም በአገራችን አንድ ሰው ሞቶ አርባ ተዝካሩ እስከሚወጣ ማታ ማታ ቤተዘመድና ጓደኛ ከስራ መልስ እየተሰባሰበ እንደሚቆዝም ከወር ባላይ በአንድነትና በደጋፊዎች ላይ የስድብ ናዳ እያወረዱ መቆዘማቸው ገርሞኝ ነው:: ምናልባትም በአንዳንድ ግለሰቦች ሌሎችም የፓልቶክ ሩሞች ያደርጉት የለም ወይ ለምን በኛ ላይ ብቻ አተኮርክ ልባል እችል ይሆናል:: ነገር ግን መልሴ ይህ ነው - ለስድብ ብቻ ብለው ቤት የከፈቱ እንዳሉ አውቃለሁ፣ እነሱ ቢሳደቡ አይደንቀኝም፣ የነጻነት ትግሉን ለማኮላሸት በወያኔ በጀት ተመድቦላቸው ዘመቻ የሚያካሂዱ ቤቶች እንዳሉም አውቃለሁ፣ እነርሱም ቢዘምቱብን አይደንቀኝም፣ ነገር ግን ካሁን በፊት ኢትዮጵያን ካራንት አፌርስን እኔ የማውቀው በብዙ በጎ ጎኑ ነውና በወያኔ ሰርጎ ገቦች ሀይጃክድ (hijacked) ካልሆኑ በቀር ይህንን ያደርጋሉ ብዬ ማመን ስላቃተኝ እስቲ እነርሱስ ከመተቸት አልፈው መተቸትን እንዴት ያዩታል? ከሚል ወገናዊነት ነው በእነርሱ ላይ ትኩረት ያደረኩት:: በተረፈ ቅንነትን የተላበሰ ግንዛቤ!

**ከድሉ ዘገየ**